የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት
The Ethiopian News Agency

# በኢትዮጵያ የሚካሄደውን የልማት ጥረት የበለጠ ለማጠናከር የተማረው የሰው ሃይል ለገጠሩ ትኩረት ሊሰጡ ይገባል

አዲስ አበባ, ሐምሌ 12 ቀን 2000 (አዲስ አበባ) -

በኢትዮጵያ የሚካሄደውን የልማት ጥረት በላቀ ደረጃ ውጤታማ ለማድረግ በአገር ውስጥ እና በውጭ ያለውን እውቀት በማቀናጀት ለመስራት ለሚደረገው እንቅስቃሴ ሁሉም መነሳሳት እንዳለበት በአንድ የፓናል ውይይት ላይ ተገለፀ፡፡

ይህ የተገለፀው የማህበራዊ ጥናት መድረክ በመባል የሚጠራው መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት " ከድህነት ወደ ልማት- እውቀትን ለትውልድ ማስተላለፍ" በሚል ትናንት በተካሄደው ውይይት ላይ ነው፡፡

የአውራጃ አስተዳዳሪ በመሆን ለረዥም ዓመታት ያገለገሉት ደጃዝማች ወልደሰማእት ገብረ ወልድ ባቀረቡት ፅሁፍ እንዳሉት በይበልጥ የተማረው የሰው ሃይል በአንፃራዊ ደረጃ የተመቻቸ የኑሮ ሁኔታ ከሚታይባቸው ከተሞች ይልቅ ድህነትን በዘላቂነት ለመግታት የገጠሩ ህዝብ የሚያካሂደውን የልማት ጥረት ለማገዝ ቆርጦ መነሳት ይኖርበታል፡፡

በኢትዮጵያ የሚካሄደው ዘርፈ ብዙ የልማት ውጥን የበለጠ እንዲጠናከር በየዘርፉ የሰለጠኑ እና የካበተ ልምድ ያላቸው ባለሙያዎች ወደገጠሩ ክፍል በመግባት ተገቢውን ድጋፍ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች 60 ዓመት በላይ በልማት ስራ ያላቸውን ልምድ ለተሰብሳቢዎቹ ያካፈሉት ደጃዝማች ወልደሰማያት የኢትዮጵያ ህዝብ ያለውን ጠንካራ የስራ አቅምና ፍላጎት የሚገቱ ሙስናንና የመልካም አስተዳደር እጦቶችን መዋጋት የሚፈለገውን ልማት እውን ለማድረግ ቁልፍ ጉዳይ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

በኢትዮጵያ የተለያዩ ብሄር ብሄረሰቦች የተለያየ እውቀት እና ልምድ ያላቸው በመሆኑ ይህንን አገራዊ እውቀት በተቀናጀ መልኩ በስራ ላይ ማዋል ልማትን በማፋጠን ድህነትን ለመግታት ያግዛል ብለዋል፡፡

ማናቸውም ዓይነት ሃይማኖት እና የዓለም ህጎች ስራን የሚያበረታቱ እንጂ ስራን የሚያጓትቱ አለመሆናቸውን ጠቅሰው በአንዳንድ ጎጂ ባህላዊ እምነቶች ሳቢያ ስራን የሚያደናቅፉ ሁኔታዎችን ለመግታት መጣር ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

የማህበራዊ ጥናት መድረክ ስራ አስፈፃሚ ዳይሬክተር ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ በዚሁ ወቅት እንዳሉት ከቀደምት ስህተቶች፣ ውጤታማ ልምዶች እና ተመክሮወዎች በመማር በአሁኑ ወቅት ያሉትን እውቀቶችና ውጤታማ አሰራሮችን ማጎልበት ይገባል፡

ደጃዝማች ወልደሰማያት በንጉሰ ነገስቱ ዘመን የአውራጃ እና የጠቅላይ ግዛት አስተዳዳሪ ሆነው ባገለገሉባቸው ዓመታት ያከናወኗቸውን ተግባራት እና ያሳለፏቸውን የተለዩ ገጠመኞች ለስብሰባው ታዳሚዎች አቅርበው ውይይት ተደርጓል፡፡

የማህበራዊ ጥናት መድረክ ከፍ ያለ የልማት ልምድ የነበራቸውን ኢትዮጵያዊያንን በመጋበዝ እስካሁን 20 መድረኮችን አዘጋጅቷል፡፡

ሪ10፡00፣ያ10፡45፣የ10፡50

---END---